## <u>የሕወሓት/ኢሕአዴግን በሕዝብ ላይ የታወጀ መዘዘኛ የሽብር ዘመቻ ማስቆም የአገር ወዳዶች የጋራ ኃላፊነት ነው!</u>

## <u>ከኢትዮጵያ አገር-አድን የቀውጢ-ጊዜ ግብረ-ኃይል የተሰጠ መግለጫ</u>

ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ/ም (ጁላይ 14 ቀን 2017 ዓ/ም)

ውድ እናት አገራችን ኢትዮጵያ በዓለማችን የገናና አኩሪ ታሪክ ባለቤት ከሆኑ ቀደምት አገሮች መኻል አንዷ ስትሆን፣ የአውሮጳና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በቅኝ-ግዛትነት ለመያዝ በተደጋጋሚ ያደረጉትን ቀጥተኛ ወረራዎችና መተናኮሎችን ሁሉ ያከሸፈች ብቸኛዋ አፍሪቃዊት አገር መሆኗ አኩሪ ታሪኳ ይመሰክራል። ለነፃነቱ ቀናዒ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው የዘመቱበትን ባዕዳን አሳፍሮ የመለሰውና ወግና ባኅሉን ጠብቆና ሉዓላዊነቱን አስከብሮ የኖረው የጋራ ማንነቱንና አንድነቱን በመኻሉ ካሉ ልዩነቶች አብልጦና ቅድሚያ ሰጥቶ ማየት በመቻሉ መሆኑ አያጠራጥርም።

ታጋሹ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ብልሹ አገዛዝ በመማረርና 'ከእሱ የባሰ አይመጣም' በሚል አጉል ተስፋ መዘናጋቱ የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር (ሕወሓት) በኢሕአዴግ ጭምብል የአገሪቱን ማእከላዊ የመንግሥት ሥልጣን እንዲቆጣጠር አስችሎታል። ይሁንናም ይኸ የእብሪት መንፈስ የተጠናወተው ጠባብ ገዥ ቡድን ይችን ጥንታዊትና ታሪካዊት አገር ለመምራት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠውን መልካም ዕድል በራሱ ጥረት ብቻ እንዳገኘውና የፈለገውንም ለማድረግ ከልካይ እንደሌለበት በመቁጠርና ያለ ምንም ይሉኝታ ጥሬ ጉልበትን በመጠቀም ላለፉት ሃያ-ስድስት ዓመታት በራሱ ዜጎች ላይ ባዕዳን እንኳን ያደርጉታል የማይባል ግፍ በመፈጸም ላይ ይገኛል። ለዚኽም ቋንቋን መሠረት ያደረገ የአስተዳደር ዘይቤን ዋነኛ የመንግሥታዊ መዋቅር አደርጃጀቱ በማድረግና ያፓርታይድ ያገዛዝ ዘዴን በመጠቀም፤ በማንኛውም አገር በሚገኝ ሕዝብ መኻል የሚኖሩ ሌሎች ልዩነቶችን ሆን ብሎ በሚከተለው መሠሪያዊ የከፋፍለህ ግዛ ዘዴዎች በመጠቀም በዜጎች ዘንድ የነበረው የአንድነት መንፈስ እንዲላላ፣ ኢትዮጵያዊ ትሥሥር እንዲሸረሸርና መቀራረብ እንዳይኖር ዋነኛ መሣሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

ይኸ ግፈኛና ሽብረተኛ ቡድን ኢትዮጵያችንን ባሕር-በር አልባ ከማድረግ ጀምሮ፣ የአገሪቱን አንጡራ መሬቶች እንደግል የቤት እቃው ለባዕዳን መለገስና ሕዝቧ በክቡር መስዋዕትነቱ ያስከበረውን ዳር-ድንበር ማስደፈር፣ የኢትዮጵያዊ ማንነትን በእጅጉ በተፈታተነና ሕዝብን እርስ-በርሱ በሚያናክስ መልኩ በዜጎች መኻል ልዩነትን መፍጠር፣ የእምነት ነፃነትን በመጋፋት ቤተ-አምልኮዎችን በፖለቲካ አቀንቃኞቹ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ማድረግ፣ የሐይማኖት መሪዎችን ማሰደድና በእስር ማማቀቅ፣ በልማት ስም የተከበሩ ጥንታዊ ገዳማትን ማራከስ፣ ማውደምና ታሪካዊ ቅርሶችን መዝረፍ፣ ዜጎችን ያለ-ምንም ሕጋዊ መሠረት ከትውልድ-ትውልድ ከኖሩበት አካባቢ በኃይል በማስለቀቅ ከውርስና ቅርሣቸው ማፈናቀል፣ በታሪካችን ታይቶም ተሰምቶም በማያውቅና ከኢትዮጵያዊ ባኅሪ በወጣና ቅጥ-ባጣ ይሉኝታ-ቢስነት ጎሠኛ-አድልዖአዊነትና ስግብግብነት እንዲሰፍን በማድረግ፣ ቅድመ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት በመጠኑ ገርበብ ብሎ የነበረውን የፖለቲካ ምኅዳር ጥርቅም አድርጎ በመዝጋት የሕዝብን ብሦት ከሚያስተጋቡ የነፃው ዜና-ዘጋቢዎች ጀምሮ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ለሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች የሚታገሉ ክፍሎችን መፈናፈኛ በማሣጣት አመራሮቻቸውን ለእስር በመዳረግ ሕዝብ ወደ አደገኛ ጠርዝ እየተገፋ አመጽ የለውጥ ማስገኛ ብቸኛ አማራጭ ሆኖ እንዲወሰድ የሚገደድበት ሁኔታን መፍጠር፣ ዜጎች፣ በተለይም ወጣቱ ክፍል በአገሩ ተስፋ እያጣ ከእናት አገሩ እንዲሰደድና ለልዩ-ልዩ ዘግናኝ አደጋዎች እንዲጋለጥ የሚያደርግ ሁኔታን በመፍጠር፣ እድገታቸውን ካልጨረሱ ታዳጊ ወጣቶች እስከ አዋቂዎች ድርስ ያሉ ኢትዮጵያዊያት በየአረብ አገሩ ለተራ የጉልበት ሠራተኝነት በገፍ እንዲወጡ በማድረግ አገራቸውን ከመልቀቃቸው በፊት ሰብዓዊ መብቶቻቸው ስለሚከበሩበት ቀርቶ በየሄዱበት ሰብዓዊ ክብራቸው ሲገፈፍና አሰቃቂ ግፍ ሲፈጸምባቸው በኢትዮጵያዊነታቸው ምንም ዓይነት ሕጋዊ ድጋፍና እርዳታ ባለማድረግ ዜጎቻችን ከሰው በታች እንዲታዩና ደመ-ከልብ እንዲሆኑ በማድረግ በየትኛውም የውጭ አገር አንገቱን ቀና አድርጎና ተከብሮ ይኖር የነበረው ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ክብርና ኩራቱን እንዲያጣ በማድረግ አጠቃላይ ኢትዮጵያን ለውርደት መዳረግ፣ በአለፉት ሃያ-ስድስት የሕወሓት-መሩ የኢሕአዴግ የግፍ አገዛዝ ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከተፈጸሙ ብዙ ግፎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ባሁኑ ጊዜ በሕወሓት አሸባሪ አምባ-ገነን አገዛዝ ሥር የምትገኘው ኢትዮጵያችን ለዜጎቿ እስር-ቤት ለገዥዎቹና ለባዕዳን ግን መክበሪያና መፈንጫ መሆኗ ከምንም በላይ በአገሪቱና በሕዝቧ እጣ-ፈንታ ላይ የሚኖረው አሉታዊ አስተጋብዖና መዳረሻ ማንኛውንም አገር-ወዳድ የምር ሊያሳስብ ይገባል።

ውድ አገራችን ለምትገኝበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ለሰብዓዊ ክብር፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነትና ለአንድነት የቆመው አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ አቅሙን አስተባብሮ አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት ካልቻለ፣ ኢትዮጵያችን እንደ አገር የማትቀጥልበትና ሕዝባችንም ለአስከፊ የእርስ-በርስ ትርምስ ሊዳረጉ የሚችሉበት አሳዛዝኝ ክስተት አይኖርም ብሎ ማሰቡ በጣም ግብዝና ሲበዛ ኃላፊነት የጎደለው ይሆናል።

ይኸ ሁሉ ግፍ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕወሓት እብሪተኛ መሪዎች ከነገ-ዛሬ ምናልባት ሊመከሩና ወደ ኅሊናቸው ይመለሱ ይሆናል በሚል ያሣየው ትእግሥት ገደቡን ሲያልፍ ለሰብዓዊ ክብሩ መቆም ነበረበት። በመሆኑም ግፍ ያንገሸገሸው ሕዝብ ትእግስቱን በተሳሳተ መልክ እንደ ፍርሃት በቆጠረው አምባ- ገነን የሕወሓት አገዛዝ ላይ በመነሣት መብቱን ለማስከበር መንቀሣቀስ ተገድዷል። ይሁንናም ለሕዝብ ብሦት ሰሚ-ጆሮ የሌላቸውና በእብሪት የተወጠሩት የሕወሓት መሪዎች መብቱ እንዲከበርለት ባዶ እጁን በወጣውና በሰላማዊ መንገድ ጥያቄውን ባቀረበው ሕዝብ ላይ፤ በተለይ በኦሮሞውና በአማራው ማህበረሰብ ላይ  የባዕድ ወራሪ ጦር እደመጣበት ሁሉ አልሞ- ተኳሽ ልዩ ኃይል የጨመረ መደበኛ ሠራዊት በማሠማራት ጭፍጭፋ አካሂዷል። አልፎም አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ መደበኛና ሕጋዊ የመብት ጥያቄዎች የተነሱባቸው አካባቢዎችን በቀጥታ በወታደራዊ እዝ ሥር እንዲሆኑ በማድረግ በሕዝብ ላይ ከዘር-ማጥፋት ወንጀል ተለይቶ የማይታይ ከፍተኛ ግፎ በመፈጸም ላይ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲኽም በአየር የተደገፈና ብረት- ለበስ (ሜካናይዝድ) ክፍሎችን የጨመረ ከፍተኛ ቁጥር ያለው እግረኛ ጦር በጎንደር እና አካባቢው አሠማርቶ የሕዝቡን ትግል ለማፈንና አዲስ-ዙር የዘር-ማጥፋት ዘመቻ ለማድረግ የተለያዩ አረመኔአዊ የጥፋት እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል።

የሕወሓት አሸባሪና ጎጠኛ የአገዛዝ ሥርዓት ጊዜ ለመግዛትና ፋታ ለማግኘት ሲል አሁንም የሕዝብን የእቢተኝነት ትግል በአጭር ለመቅጨትና ምን-ጊዜም አጥብቆ የሚፈራውንና የሚያባንነውን የሕዝብ አንድነት ለማጨናገፍ አንዳንድ አታላይና አዘናጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ሲውተረተር እያየን ነው። ቅጥፈትና ማስመሰል፣ መሠሪነትና አሸባሪነት ባኅሪያቸው የሆነው የሕወሓት እብሪተኞች፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን ጭምር አስረው እያሰቃዩ ባሉበት ሁኔታ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው በአገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ እስረኛ የለም ይሉናል።

ባረጀና ባፈጀ 'የከፋፍለህ ግዛ' ስሌት ሕዝብን እርስ-በርሱ ለማናከስና የሕዝብን ትኩረት ለማስቀየር በማሰብ በ 'ልዩ ተጠቃሚነት መብት' ስም አዲስ አበባን በተመለከተ 'ረቂቅ አዋጅ አወጣሁ'፣ መሪዎችን አስሮና ሕዝብ ድምፁን በነፃነት ማሰማት በማይችልበት ሁኔታ፣ ዴሞክራሲን ለመገንባት ከተቃዋሚው ጋር ድርድር ላይ ነኝ፣ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ መደበኛ ሠራዊቱን አዝምቶ ዘር-አጥፊ ጭፍጨፋ እያካሄደ፣ አሸባሪዎችን ለመቋቋም እየሞከርኩ ነው፣ አገሪቱን ለገዥው አውራዎችና ለባዕዳን ብዝበዛ አመቻችቶና ሕዝብን የበይ- ተመልካች በማድረግ፣ ስለ እድገትና ብልጽግና፣ ወዘተ... ይወሻክታል።

'የሕወሓት አገዛዝ በቃኝ! መብቴን ማስከበር አለብኝ!' ብሎ የተነሣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በአገዛዙ አስመሣይ ህቶትም ሆነ ጭካኔ የተሞላበት የሽብር ዘመቻ አይንበረከክም። የሕዝባዊ እምቢተኝነትን ትግል በኃይል ለማፈን መሞከር ችግርን ይበልጥ ከማባባስና ከማወሳሰብ ውጪ ዘለቄታዊ ውጤት እንደማይኖረው የአዛዙ ግብዝ መሪዎች የተረዱት አይመስልም። ምንም እንኳ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስም ወታደራዊ አገዛዝን በሕዝብ ላይ በመጫን በተወሰዱ የግፍ እርምጃዎች ምክንያት የሕዝባዊ እምቢተኝነቱን እንቅስቃሴ ለጊዜው ቢያፍነውም፣ አገዛዙ ሰሞኑን በተለይ በንግዱ ማኅበረሰብ ላይ የጫነውን ጭፍን የግብር ጭማሪ በመቃወም ሕዝብ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በመጣስ በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በማድረግ ላይ ነው። እነኚህ የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎች በየተራ ተነስተው አገዛዙ በሚወስዳቸው የግፍ እርምጃዎች በየተራ እንዳይከስሙ አገር-አቀፍ ይዘትና ብሔራዊ ቅርጽ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ለዚኽም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች አስቸኳይ ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጡና ከሕዝብ ጎን ሊቆሙ ይገባል።

የኢትዮጵያ አገር-አድን ግብረ-ኃይል በሕወሓት የሚመራው የኢሕአዴግ የሽብርና የግፍ አገዛዝ ዕድሜ የሚኖረውና በአኳያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰቆቃ ሊቀጥል የሚችለው አገር-ወዱ የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይል ከተለመደው ጊዚያዊ ጥቅምን ካስቀደመ አደረጃጀት ተላቅቆ እና ከጠባብ የቡድናዊነትም ሆነ የድርጅት አጥር ወጥቶ አገርንና ሕዝብን መታደግ የሚችል አዲስ አገራዊና ብሔራዊ የኃይል አሠላለፍ መያዝ ሣይችል ሲቀር ብቻ ነው። በመሆኑም፣ ኢትዮጵያችንን ከብተና እና ሕዝባችንንም ከተደገሰለት የእስ-በርስ ትርምስ አደጋ ለመታደግ የኢትዮጵያውያን አገር-ወዳዶችና የአንድነት ኃይሎች አገራዊ ጉባዔ በአስቸኳይ እንዲካሄድና ትርጉም ያለው ብሔራዊ አማራጭ ኃይል እንዲፈጠር እነሆ ለሚመለከተው ሁሉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ዘመቻዎች እናደርጋለን።

ከጥር ፭ እስከ ፮ ቀን ፪ ሽህ ፱ ዓ፡ም (ጃንዋሪ 13-14 ቀን፤ 2017 ዓ፡ም) በዋሽንግተን ዲሲ ሁሉን-አቀፍ የምክክር ጉባዔ በዘጠኝ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች መካከል በተደረገው ውይይት ላይ በተደረሰው ስምምነት መሠረት፤ 1ኛ/ የአገር አድን የቀውጢ ጊዜ ግብረ ኃይል ማቋቋማችን፤ 2ኛ/ ሁነኛ የአንድነት ኃይሎች አማራጭ በአጭር ጊዜ የማውጣት ሂደት ላይ የሚሠራ አንድ ልዩ ኮሚቴ እንዲሰየም መወሰናችንን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ይፋ እነዳደረግን የሚታወስ ነው። በወቅቱ ስምምነት ላይ የደረስነው የ9 ድርጅቶች ስም ዝረዝር፤ 1ኛ/ ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት 2ኛ/ቱሳ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት 3ኛ/የአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ 4ኛ/የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ 5ኛ/የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አንድነት ንቅናቄ 6ኛ/የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት 7ኛ/የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ 8ኛ/የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ 9ኛ/ዳግማዊ አርበኞች ንቅናቄ ..ነን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብርና አንድነት በተለመደው የልጆቿ ኅብረት ይጠበቃል!!**

**የኢትዮጵያ አገር-አድን የቀውጢ-ጊዜ ግብረ-ኃይል**